የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፷፩
አዲስ አበባ-ሐምሌ ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No. 61
ADDIS ABABA- 2nd August, 2004

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፯/፲፱፻፺፮ዓ.ም

ከቱኒዝያ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን በሁለትዮሽ ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ .........ገጽ ፪ሺ፰፻፴፰

CONTENTS

Proclamation No. 417/2004

Investment Reciprocal Promotion and Protection Agreement with the Republic of Tunisia Ratification Proclamation ............. Page 2838

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፯/፲፱፻፺፮

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በቱኒዝያ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን በሁለትዮሽ ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አ ዋ ጅ

በቱኒዝያ ሪፐብሊክ መንግሥትና በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን በሁለትዮሽ ለማስፋፋት እና ዋስትና ለመስጠት ታህሣሥ ፭ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ስምምነት በአዲስ አበባ የተፈረመ ስለሆነ፤

ስምምነቱን በሚገባ ሥራ ላይ ለማዋል በተዋዋይ ሀገር ህጎች መሠረት ስምምነቱ መጽደቁን የሚያረጋግጡ ሰነዶች በዲፕሎማቲክ አካላት አማካኝነት ልውውጥ ከተደረገ በኋላ እንደሆነ በስምምነቱ ስለተገለፀ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት ከዚህ እንደሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO. 417/2004.

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT ON THE RECIPROCAL PROMOTION AND PROTECTION OF INVESTMENT BETWEEN THE GOVERNMENTS OF FEDERAL DEMOCATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE REPUBLIC OF TUNISIA

**WHEREAS,** the Agreement on the Reciprocal Promotion and Protection of Investment between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Tunisia is signed in Addis Ababa on December 14, 2000;

**WHEREAS,** it is stipulated in the Agreement that it shall enter into force on the date of exchange of instruments of ratification through diplomatic channel;

**WHEREAS,** the House of the People's Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has rarified the said Agreement at its session held on 6th day of July, 2004

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub Article (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows;

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ከቱኒዝያ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን በሁለትዮሽ ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፯/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪. ስምምነቱ ስለመጽደቁ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቱኒዝያ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል ኢንቨስትመንትን በሁለትዮሽ ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት በአዲስ አበባ ከተማ ታኅሣሥ ፭ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም የተፈረመው ስምምነት ፀድቋል::

**፫. የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኃላፊነት**

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ስምምነቱን በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል::

**፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት



**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as "Investment Reciprocal Promotion and Protection Agreement with the Republic of Tunisia Ratification Proclamation No. 417/2004."

**2. Ratification of the Agreement**

The Agreement on the Reciprocal Promotion and Protection of Investment signed in Addis Ababa on 14th of December 2000 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Tunisia is ratified.

**3. Power of the Ethiopian Investment Commission**

The Ethiopian Investment Commission is hereby empowered to implement this Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication on the Federal Negarit Gazeta

**Done at Addis Ababa, this 2nd day of August, 2004.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**